# የሕሊና እና አካላዊ እስረኛው የትግራይ ህዝብ

**ተስፋሁን አረጋይ**

**November 21, 2018**

ማን ነው እስረኛ ያደረገው? የ **VOA** ን ዘገባ መሰረት ያደረገ መጣጥፍ

ይህ ከጭንቀት ያልወጣ ትውልድ ወያኔ/ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ቦኋላ ብቻ አይደለም ገና ደርግ በስልጣን ላይ  በነበረበት ወቅትም ሁለት የማይመረጡ ምርጫዎችን ተሸክሞ ይሰቃይ ነበር። በአንድ በኩል የደርግ መንግስት በጭፍን በሚወስዳቸው እርምጃዎች አገሪቱ የምታጣቸውን ልጆችዋን፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ በደርግ ግትርነት እና ድንቁርና በሚራመደው ፖሊሲ የሃገሪቱ የወደፊት እጣ ፈንታ ወደ ከፍተኛ አደጋ ይጓዝ ስለነበር ከምር የሚያስጨንቅ ጊዜ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ አገሪቱን ለመበታተን የተደራጁት የጠባብ ብሄርተኛ ሃይሎች እያጎለበቱ በመምጣታቸው የሃገሪቱ እና የህዝብዋ እድል ወደ ከፍተኛ አደጋ እየወደቀ ስለነበር ሌላው ከፍተኛ ጭንቀት ነበር፤  ከዚህም ጋር ተያይዞ እነዚህ ጠባብ ሃይሎች "ብሄራችን" በሚሉት ህብረተሰብ ውስጥ የሚፈጠሩትን ሃገር ወዳዶች እና ዴሞክራቶች እየመነጠሩ ያጠፉዋቸው ስለነበር አደጋውን የተገነዘበው ክፍል ምን ያህል ይጨነቅ እንደነበር ለብዙዎች እምብዛም ግልጽ አልነበረም። ዛሬ በሃገራችን የምናየው የጠባብ ብሄርተኞች እብሪት እና የዘራፊዎች የተወሳሰበ መረብ የዚያ የዘቀጠ ፖለቲካ ውጤት ነው።

እንደተፈራው ደርጎች ያን ሁሉ ጥፋት ካጠፉ ቦኋላ አንድም የደርግ አባል መስዋእትነት ሳይከፍል መሪያቸውን ሸኝተው የገደሉበትን መሳሪያ እየደረደሩ ተሰልፈው ለነወያኔ እጃቸውን ሰጡ። ይህም በመሆኑ ላለፉት 27 ዓመታት በተደራጁ የጠባብ ብሄርተኛ እና የማፍያ ቡድኖች የኢትዮጵያ ህዝብ ከፍተኛ ጭፍጨፋ እና ዘረፋ ሲካሄድበት ማየት ብቻ ሳይሆን እንበታትናችኋለን እያሉን ሲያስጨንቁን ቆይተዋል። በወገኖቻችን ላይ ስለተፈጸመው ግፍ በሃገራችን ውስጥ ስለተደረገው  ዘረፋ ዛሬ እኔ መናገር የለብኝም፤ ETV ያለ ህፍረት እየዘገዘገበው ነው ፤ ባለስልጣኖቹም እየተናዘዙት ናቸው። ዛሬ በሚሰማው እና በሚታዩት ዘገባዎች የማያዝኑ እና የማይበሳጩ ካሉ "የቀን ጅቦች" ተብለው በጥሩ ቋንቋ የተገለጹት ሰዎች ብቻ ናቸው። አዎ የቀን ጅቦቹ አሁንም ባለማፈር በአንዳንድ ሚድያዎች ሌላ የጥፋት እሳት ለመለኮስ እየዘላበዱ ቢሆንም ETV ገና አልዘመተባቸውም አልደፈራቸውም፤ ስለሆነም አሁንም እንደልባቸው የጥፋት መርዛቸውን በመርጨት ላይ ካሉት አሳፋሪ "ምሁር"  የአንዱን አስተያየት መሰረት በማድረግ በዝች ጽሁፌ መተቸት እፈልጋለሁ።

በ-11/14/2018  የ VOA ሬዲዮ የነ "ሜ/ጀ" ክንፈ ዳኘውን እና መሰሎቹን መያዝ አስመልክቶ የህዝብ አስተያየት ለማሰማት ከጠየቃቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ የመቀሌው ዩንበርስቲ የፖለቲካል ሳይንስ እና ስትራቴጅክዊ ጥናቶች አስተማሪ ናቸዎ  የተባሉት

አቶ ሠይፈ ኃይሉ ናቸው፤ አቶ ሠይፈ "እርምጃው የትግራይን ሊህቃን ለማጥፋት ያነጣጠረ ነው" በማለት ንግግራቸውን ሲያጠናክሩ "በአንድ ብሄር ላይ ያነጣጠረ ብሄሩን ግዛቱን እና መንግስቱን ለማዳከም በውጭ ሃይሎች ጭምር የተመከረበት እና የሚደገፍ ሥራ ነው" ከማለት አልፈው "የዘር ማጥፋት (Ethnic classy) እየተካሄደ ነው" በማለት መረር አድርገው ሲናገሩ ለሰማቸው በጣም አስደንጋጭ ነበር። ለመሆኑ ግለሰቡ በእርግጥ ethnic classy የሚለውን ቃል ትርጉም ያውቁታል ወይ ያስብላል፤ እኒህ ግለሰብ በ VOA ቀርበው እንዲህ የሚናገሩ ከሆነ በአካባቢያቸው ባሉት ሚዲያዎች እና በሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ ምን ዓይነት መልዕክት እያስተላለፉ ህዝብን በመቀስቀስ ላይ መሆናቸውን ለመገመት አያዳግትም። እንግዲህ አስቡት እኒህ ሰው በሺ የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ያስተምራሉ እነዚህ በሺ የሚቆጠሩ ተማሪዎች ደግሞ በሚልዮን ከሚቆጠረው ኅ/ሰብ ጋር በቀላሉ መገናኘት ይችላሉ፤ እንግዲህ አስቡት በእንደዚህ አይነት "ሙህራን" ነው የትግራይ ህዝብ የቁም እስር እንዲሆን ትምህርት የሚሰጠው፤ እንግዲህ አስቡት እንዲህ ዓይነት ሙህር ተብየዎች ናቸው ትግራይን የሚያስተዳድሩትን የፖለቲካ መሪዎች እያስተማሩ የሚያስመርቁት፤ እንግዲህ አስቡት እንደዚህ አይነት ሙህር ተብየዎች ናቸው የወያኔን መሪዎችን እና የትግራይን ሹሞችን የሚያማክሩት። ይሄው ዶ/ር ደብረ ጽዮንም የተማሩትን ትምህርት ተቀብለው በሁለተኛው ቀን እነዚህን ቃላት በመጠቀም በመንግስታዊ መግለጫቸው የትግራይን ህዝብ እያስፈራሩት ነው።

የፌደራሉ አቃቢ ህግ የሚወስደው እርምጃ ዘርን ወይም ብሄርን ወይም ፖለቲካን መሰረት ያደረገ ሳይሆን ወንጀልን መሰረት አድርጎ የሚካሄድ እርምጃ መሆኑን እንደገለጹት እኛም በተግባር እንዳየነው የሚባረሩት እና የሚታሰሩት የተለያዩ ብሄረሰብ ተወላጆች መሆናቸውን እያየን ነው፤ እኒህ "ሙህር" ተብዬ ግን ይህን መረጃ ለመስማትም ሆነ ለማየት አዕምሮአቸው ቦታ የለወም፤ የጠባብ ብሄርተኝነት ችግር እንደዚህ ነው ከራሱ ብሄር ውጭ ሌላውን አያምንም ሌላውን አይሰማም። ግን አሁን እኒህ ሰው ምሁር ሊባሉ ነው? አየ ትግራይ ለመላው ኢትዮጵያ ህዝብ ትልቅ ራዕይ ሰንቀው በጀግንነት የተሰውት እነ ተስፋዬ ደበሳይ(ዶ/ር) እነ ዮሴፍ አዳነን እነ ብርሃነ መስቀልን ረዳ እንዳልተወለዱብሽ ዛሬ ህዝብን ከህዝብ ለማጨራረስ ሃላፊነት የማይሰማቸው "የፖለቲካ ሙህራን" ነን የሚሉ አጓጉሎችን ሰንሰማ እንዴት ያሳዝናል፤ የነሱዎቹስ "ሰማዕታትስ" ይህን አሳፋሪ ታሪክ ቢሰሙ መስዋዕትነታቸው እንዴት ይጸጽታቸዋል።

የትግራይ ህዝብ እንደነ እስከንድር ነጋ አንዱዓለም አራጌ እና ርዕዮት አለሙ እግር እና እጁን ብቻ አልታሰረም፤ በየቀኑ የሚቀርብለት መረጃ ህሊናውን እስረኛ የሚያደርግ ነው፤ በየጊዜው የሚሰጠው ቅስቀሳ ሌላውን ህብረተሰብ እንዲፈራ እና እንዲጠራጠር የሚያደርግ ነው። ይህን ሰብሮ ለመውጣት እና የትግራይ ህዝብ ከሌሎቹ ወገኖቹ በእኩልነት በትግሉ እንዲሳተፍ እና እንደሌሎቹ የነጻነት ጮራ እንዲፈነጥቅለት ሚዲያዎች ትልቅ ስራ ይጠበቅባቸዋል። በአሁኑ ወቅት የአማራው ወይም የኦሮሞው TV እና ሬዲዮ የሚያደርገውን ዓይነት አስተዋጽዖ የትግራይ TV እና ሬዲዮ ስለማያደርግ ESAT እና ሌሎቹም ሚድያዎች በዚህ ዙርያ ልዩ ትኩረት በመስጠት እየጎረፈ ያለውን መረጃ በትግረኛ በመተርጎም ለትግራይ ህዝብ ለማድረስ ቢሞከር አላስፈላጊውን ጥፋትን ማስወገድ እንችላለን። ETV ሰፋ ያለ የትግረኛ ፕሮግራም ቢኖረው የአማራው እና የኦሮሞው ሚዲያዎችም የተወሰነ የትግረኛ ክፍለ ጊዜ በፕሮግራማቸው አስገብተው በዚህ ዙሪያ ትልቅ ስራ መስራት ያለባቸው ወቅት አሁን ነው።(የትግራይ TV የአማርኛ ፕሮግራም አለው)

ለኢትዮጵያዊነታችን በጽናት የምንቆም ሃይሎች የትግራይን ህዝብ ጉዳይ በጥንቃቄ ልንይዘው ይገባል፤ የትግራይ ህዝብ ስንልም ሰፊውን አርሶ አደር እና ሰርቶ አደሩን እንጅ ከወያኔ ሃርነት የሚያገኘው ጥቅማ ጥቅም እንዳይጎድልበት የወያኔ ሀርነትን ወንጀል

እና ዘረፋ ለመደበቅ በአንዳንድ ሚድያዎች ብቅ እያሉ የሚያቃጥሉነን አሳፋሪ ባለጌዎች፦ "ሙህራን" እና ፖለቲከኞቹን አይደለም። ስለዚህ ሚድያዎቹም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች መስራት የሚገባቸው ጠንካራ ስራ ቢኖር የትግራይን ህዝብ ከአድር ባዮቹ "ሙህራን" እና ከወያኔ ሀርነት ህሊናውይ እና አካላዊ እስር ቤት አውጥቶ ከሌሎቹ ወገኖቹ ጋር እንዲቀላቀል ማድረግ ነው፤ እነዚህ ሃይሎች ሌት ተቀን በህዝቡ ውስጥ ተሰግስገው ያላቸውን የሚድያ ፍጆታም በሙሉ በመጠቀም በትግራይ ህዝብ ውስጥ ትልቅ ስጋት እና ጥርጣሬ እንዲፈጠር በማድረግ ላይ ያሉትን ቅስቀሳ የሚያፈርስ በቂ ስራ በሚገባ አልተሰራም። እነ OMN የኦሮሞን ወጣት ለማንቀሳቀስ ምን ያህል ስራ ይሰሩ እንደነበር አንርሳው ይህን ልምድ ከተጠቀምንበት ውጤታችን በአጭር ጊዜ ውስጥ እናያለን። ስለዚህ የወያኔን እና ያድርባይ ሙህራኑን መረብ በመበጣጠስ የትግራይን ህዝብ ከእስርቤት ለማውጣት ሰፊ እና ጠንካራ ስራ እንስራ።

በነ አሉላ አባ ነጋ በነ አውዓሎም አኩሪ ታሪክ የሚኩራሩት የትግራይ ልጆችም የአባቶቻቸውን ታሪክ የሚያበላሽ ስራ እየተሰራ ተኝተው ማደር የለባቸውም፤ የሚመጣውን መስዋዕትነት ሳይፈሩ ግንባር ቀደም ሆነው ወገኖቻቸውን ከዚህ ባርነት ማላቀቅ አለባቸው፤ እንደ OMN አክቲቢስቶች ህዝባቸውን በራሱ ቋንቋ በመቀስቀስ ወያኔ ሀርነት ትግራይ የትግራይን ህዝብ ከሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ነጥሎ የቁም እስር ያደረገው መሆኑን ሊያስረዱት ይገባል፤ ይህን የማያደርጉ ሙህራን ግን በዚህ ስህተት የሚፈጠር ችግር ቢኖር በሚደርሰው ጉዳት ዕድሜያቸውን በሙሉ በመጸጸት እድሚያቸውን በሙሉ ያፍራሉ፤ ስለዚህ ማናቸውንም የመገናኛ ብዙሃን በመጠቀም በትግረኛ ቋንቋ የወያኔ ሀርነትን የግፍ አገዛዝ እና የዘረፋ ታሪክ  የትግራይ ህዝብ እንዲያውቀው ለማድረግ መድፈር አለባቸው፤ ሚድያዎችም ይህን እድል በሰፊው ሊሰጥዋቸው ይገባል።

በመጨረሻም ይህን የጥፋት ሃይል ለሚደግፉትም ሆነ በአድርባይነት ድምጻቸውን አጥፍተው ለተቀመጡት ወይም በተዘዋዋሪ ለሚደግፉት "ሙህራን" የምለው ቢኖር፦ይህ ለውጥ ምንም ሃይል አያቆመውም፤ ከአሁን ቡኋላ የኢትዮጵያ ህዝብ ያለፈውን የመከራ ቀንበር ለመሸከም ህሊናው አይፈቅድም፤ በቃ ጣልያን በአምስት ዓመት ከፈጸመብን ያልተናነሰ መከራና ስቃይ ከዘረፋ ጋር በትዕግስት ተቀብለናል፤ ግን ይህ መስዋዕትነት የተከፈለው ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን ከማስቀጸል አንጻር በመሆኑ አይጸጽተንም፤ አሁንም ነገም ሁሉም የኢትዮጵያ ህዝብ መብቱ ተከብሮለት በእኩልነት የምንኖርበት ስርዓት እንዲገነባ ጠንካራ አገር እንዲኖረን የምንከፍለው መስዋዕትነት ካለ በጸጋ እንቀበለዋለን እንጅ ፈርተን አንሸሸውም።

ተስፋሁን አረጋይ

(tgebremichael@medshare.org)

November 2018